## የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡— በአገሮች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረግ ፡ የሙሉ ፡ ገዥ ነት ፡ መረካከብ ፡

ከሳሽ ፤ ትሪንጋሌ ፡ ካርሜሎ ፡ ቴሬዛ ፡
ተከሳሽ ፤ ማልተስ ፡ ቪንቸንዞ ፡
የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺/፹፪

ከፋሲል ፡ ናሆም ።

በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሳሽ ፡ ትሪንጋሌ ፡ ካርሜሎ ፡ ቴሬዛና ፡ ተከሳሽ፡ማልቴስ ፡ ቪን ቼዞ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ሥርዓት፡ ጋብቻቸውን፡አከበሩ ። ቀጥሎም፡ጋብቻው፡ በአሥመራ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ተመዘገበ ። በነሐሴ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሳሽ ፡ ለአስመራ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋብቻው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ እንዳልነበረ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆጠር ፡ ጋብቻውም ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መመዝገቡ ፡ የሚያስከትለው ፡ የሕግ ፡ ኃይል ፡ እንዲፈርስና ፡ የክብር ፡ መዝ ገቡም ፡ ሹም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ መዝገቡን ፡ እንዲያርም ፡ ትዕዛዝ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ አቤቱታ ፡ አቀረቡ ።

በዚህ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረቡትን ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ለመረዳት ፡ የነገሩን ፡ ታሪ ካዊ ፡ መነሻ ፡ ከስር ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኢጣሊያና በመንበረ ፡ ጵጵስናው ፡ መካከል ፡ ውል ፡ (ኮንኮርዳት) ተፈረመ ። በዚሁ ፡ ውል ፡ መሠ ረት ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ በኢጣሊያን ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ በሮማዊት ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመውን ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ ረገድ ፡ በይፋ ፡ እንዲያውቅ ፡ ተስማማ ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ ይህንኑ ፡ ውል ፡ ለማስፈጸም ፡ በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፹፪ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ደነገገ ። ይህም ፡ ሕግ ፡ በመንበረ ፡ ጵጵስናውና ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ በኢጣሊያ ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ሁሉ ፡ በኤርትራም ፡ ጭምር ፡ ተፈጻ ሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ አደረገ ።

ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበራት ፡ የሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ሥልጣን ፡ በመስከ ረም ፡ ፲ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኢጣሊያና ፡ በአራቱ ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ በተፈረ መው ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ (ትሪቲ) ፡ መሠረት ፡ ተፈጸመ ።[1] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበራትን ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ የመቆጣጠር ፡ ተግባር ፡ የአቆመ ችው ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነበር ። በሰላሙ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የሚከተለው ፡ ቃል ፡ ይገ ኛል ፡ "የመጨረሻው ፡ የኤርትራ ፡ ጉዳይ ፡ የሚወሰነው ፡ በሶቭየት ፡ ኅብረት ፡ በታ ላቋ ፡ ብሪታንያ (ዩናይትድ ፡ ኪንግደም) ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስና ፡ በፈረንሣይ ፡ መንግ

1. "ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ያላትን ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ለቃለች" አንቀጽ ፡ ፳፫ (፩) የሰላሙ ፡ ውል ።

ሥት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ የሚደረገው ፡ የአሁኑ ፡ ውል ፡ ከሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፣ የተባሉት ፡ መንግሥታት ፡ የካቲት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባወጡት ፡ የጋራ ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ በተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ነው ።”[2]

እነዚህም ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ የኤርትራ ፡ ጉዳይ ፡ ምን ፡ ላይ ፡ እንደሚ ቆም ፡ ባለመስማማታቸው ፡ የወደፊቱን ፡ የኤርትራን ፡ አቋም ፡ የመወሰኑ ፡ አሳፊነት በጋራ ፡ መግለጫው ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፣ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፣ ለተባበ ሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ተላለፈ ። የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ጉባዔም ፡ በታህሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኤርትራና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በፌዴራሲ ዮን ፡ መቀላቀል ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ውሳኔ ፡ አሳለፈ ። የዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ሕጋዊ ፡ ጽሑፍ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኤርትራ ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጸደቀ ። በኋላም ፡ በህዳር ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትዕዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፳፯/፶፭[3] ፡ በኢትዮ ጵያና ፡ በኤርትራ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ፌዴራሲዮን ፡ አፍርሶ ፣ ኤርትራ ፡ የኢትዮጵ ያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንድትሆን ፡ አደረገ ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ የተነሳው ፡ ዋና ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ የ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢጣሊያና ፡ የመንበረ ፡ ጵጵስናው ፡ ውል ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ቴሬዛና ፡ ቪንቸንዞ ፡ በተጋቡበት ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ጸንቶ ፡ የሚ ቆይበት ፡ ምክንያት ፡ ነበረው ፡ ወይ ፡ የሚል ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የፍት ሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጋብቻን ፡ በማፍረስ ፡ ረገድ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ እንዲሰሩ ፡ ግዴታ ፡ ይኖርባቸዋል ። ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ምህረቱ ፡ ውል ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንቶ ፡ ከነበረ ፡ ይኸንን ፡ ጋብቻ ፡ ለማፍ ረስ ፡ የሚቻለው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሲፈቅዱ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፈቃድ ፡ ከነዚህ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተሰጠ ፡ አይመስልም ።

በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበራትን ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ለኤ ርትራና ፡ ለፌዴራሲዮኑ ፡ መንግሥት ፡ ማስረከቧ ፡ ይታወሳል ። ስለዚህ ፡ ውሉ ፡ እስ ከተባለው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ አልነበረም ፡ ለማለት ፡ የሚረዱት ፡ የነዚህ ፡ ተረካቢ ፡ መንግሥታት ፡ መብቶችንና ፡ ግዴታዎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ፅንስ ፡ ሐሳቦች ፡ ናቸው ። ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ አከራካሪ ፡ ነገር ፡ ሲያትት ፡ “በአገሮች ፡ መካከል ፡ በሚደ ረግ ፡ የሙሉ ፡ ገዥነት ፡ አረካከብ ፣ አስረካቢው ፡ አገር ፡ አስቀድሞ ፡ የፈረማቸውን ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ተረካቢው ፡ አገር ፡ ለመረከብ ፡ አይገደድም ፡ የሚል ፡ የማያጠ ራጥር ፡ መሠረታዊ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ አለ” ብሎ ፡ ጽፏል ። በተጨማሪም ፣ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚከተለውን ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ። “የአንዱን ፡ መንግሥት ፡ የገዥ ነት ፡ ሥልጣን ፡ ማስፋት ፡ የሌላውን ፡ መንግሥት ፡ የገዥነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚያ ጠብ ፡ ወሰን ፣ ውጤት ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፣ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ መንግ ሥት ፡ ሲስማማ ፡ ብቻ ፡ ነው ፣ እንጂ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመቋቋሙ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ሕግ ፣ መሠረት ፡ አይደለም ።”

---

2. አንቀጽ ፡ ፳፫ ፣ ፫ ፣ (፫) ፣ የሰላሙ ፡ ውል ።
3. የኤርትራን ፡ የፌዴራል ፣ አስተዳደር ፣ ለማስቀረትና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፣ የአንድነት ፣ አስተዳደር ፣ ለመተካት ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍ ፫ ፣

ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ ውሉ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ሊጸና ፡ የሚችለው ፡ ኤርትራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ሥር ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፡ ብታጸድቀው ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ። በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡[4] መሠረት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶችን ፡ ማጽደቅ ፡ ለፌዴራሲዮኑ ፡ ሙሉ ፡ ገዥ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ ነበር ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ይህን ፡ ውል ፡ ባለማጽደቁ ፡ ይህ ፡ በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኢጣሊያና ፡ በመንበረ ፡ ጵጵስናው ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ አይጸናም ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሉ ፡ ከ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ መቸ ፡ ተፈጻሚነትን ፡ እንዳጣ ፡ ማለት ፡ የኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ የመቆጣጠር ፡ ተግባር ፡ ባቋረጠበትና ፡ ደንቧም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ባቆመበት ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡ የ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ሲጸና ፡ ወይም ፡ የእንግሊዝ ፡ የሲቪል ፡ አስተዳደር ፡ ተፈጽሞ ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲመሠረት ፡ መሆኑን ፡ አልገለጸም ። ጋብቻው ፡ የተፈጸመው ፡ በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሳያትት ፡ አልፏል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተግባሩን ፡ ያከናወነው ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ሐተታ ፡ የቀረበለትን ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ የለበትም ፡ በሚለው ፡ ፅንሰ—አሳብ ፡ በመመራት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ባይሰጥም ፡ እንኳ ፡ የጥያቄውን ፡ አሳሳቢ ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ። "ኢጣሊያ ፡ ሙሉ ገዥነቷን ፡ ከለቀቀችበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘውዱን ፡ በመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ተረከበበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ውሉና ፡ ከውሉ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት የነበራቸው ፡ ንዑሳን ፡ ደንቦች ፡ ጸንተው ፡ ነበሩ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ።"

ከ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ውሉ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ውድቅ ፡ መሆኑ ፡ እና ፡ ይሠራበት ፡ እንዳልነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ "አንድ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቆጠረው ፡ ውሉን ፡ ባደረጉት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ ነው።"[5] ኤርትራም ፡ በፌዴራሲዮኑ ፡ መሠረት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በመዋሃዱ ፡ የአንድ ፡ ልዩ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ አካል ፡ ክፍል ፡ ሆነች ። በመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ፅንስ—አሳቦች ፡ መሠረት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ አካል ፡ ሌላው ፡ መንግሥት ፡ በገባበት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ። ስለዚህ ፡ ውሉ ፡ ከ፲፱፻፵፭፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ይሠራበት ፡ አልነበረም ። ይሁንና ፡ በኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ መፈጸምና ፡ በፌዴራሲዮን ፡ መመሥረት ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ ይሠራበት ፡ አልነበረም፡ለማለት ፡ ይቻላልን?

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ አልገለጸም ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ በመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ፅንስ—ሐሳቦች ፡ የሚደገፍ ፡ አይመስልም ። የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚስማሙበት ፡ አንድ ፡ ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ የአንድን ፡ ግዛት ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ የሚረከበው ፡ ሀገር ፡ ያስረካቢውን ፡

4. የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ (፩)
5. የኢንተርናሲዮናል ፡ ቋሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰርተን ፡ ጀርመን ፡ ኢንተረስትስ ፡ ኢን ፡ ፖሊሽ ፡ አፐር ፡ ሴሌሺያ ፡ በሚለው ፡ ጉዳይ ፡ ፔ- ሴ- አይ- ጄ- ሴር ኤ- ቍጥር ፯ ፡ ገጽ ፡ ፳፱ ፡ (፲፱፻፳፮ ፡ እ- ኤ- አ-)

አገር ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ጨምሮ ፡ አይረከብም ። ስለዚህ ፡ ያስረከቢው አገር ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ (ፓብሊክ ፡ ሎው) ፡ የአገሪቷ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጸንቶ ፡ ሊቆይ ፡ አይችልም ።[6] በአገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ በነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ።[7] ስለዚህ ፡ የአሁኑ ፡ ውል ፡ ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበራትን ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ካጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ በኢጣ ሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ መፈጸምና ፡ በፌዴሬሲዮኑ ፡ መመሥረት ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ የማይሠራበት ፡ ምክንያት ፡ የኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት በእንግሊዝ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ በመተካቱ ፡ ነው ።[8]

እስካሁን ፡ የተመለከትነው ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ "ተዛ ማጅ ፡ ደንቦች" ፡ ብሎ ፡ የጠቀሰው ፡ የ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቊጥር ፡ ፳፻፵፪ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ነው ። ይህ ፡ በሃይማኖት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ መፍረስ ፡ የለበትም ፡ የሚለው ፡ ክርክር ፡ የተመሠረተው ፡ ከ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውል ፡ ይልቅ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

የፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ውሳኔ ፡ የሚለው ፡ ውሉ ፡ የማያገለግል ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቊጥር ፡ ፳፻፵፪ ፡ ሕግም ፡ በኤርትራ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ነው ። አስተያየቱን ፡ ለመደገፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ መስሎ፡ የሚታየውን ፡ አንድ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያ ፡ የሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ ጠቅሷል ። ይኸውም ፡ "በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሲሰረዝ ፡ በውሉ ፡ ምክን ያት ፡ የወጡ ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይሰረዛሉ ። ለነኚህ ፡ ደንቦች ፡ መሠረዣም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ማረጋገጫ ፡ ለመስጠት ፡ ደንብ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፡" ፡ የሚል ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ነገሩን ፡ ከሚፈርስ ፡ ጣራ ፡ ጋር ፡ በማነፃፀር ፡ ተናግሯል ። አንድ ከጣራው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ የመብራት ፡ ማንጠልጠያ ፡ ጣራው ፡ ሲወድቅ ፡ አብሮ ፡ መውደቁ ፡ አይቀርም ፡ ብሏል ። ይህ ፡ ምሳሌ ፡ የአቀራረብ ፡ ውበት ፡ ቢኖረውም ፡ ጉዳዩን ፡ በትክክል ፡ አያስረዳም ። በትክክለኛ ፡ የአስተሳሰብ ፡ ዘዴ ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቆይበት ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ በውሉ ፡ ምክንያት ፡ የተደነገገው ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መቆየት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያስፈልጋል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። የጀርመን ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ አጋጥሞት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ በመቀበል ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ "በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሥምምነቱ ፡ ጽኑነት ፡ ቢፈጸምም ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉት ፡ ደን ቦች ፡ የአገሩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በሆኑበት ፡ መጠን ፡ ጽኑነታቸውን ፡ ሳያጡ ፡ ይቆያሉ ። በኢንተርናሲዮናል ፡ ረገድ ፡ ጽኑነትን ፡ ማጣት ፡ ውስጣዊ ፡ ጽኑ ነትን ፡ ላይነካ ፡ ይችላል"[9] ፡ የሚል ፡ ነው ። (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ።

6. አር ፡ ፒ ፡ ኤ ፡ ኮኔል ፡ ዘሎው ፡ አቭ ስቴት ፡ ሳክሴሽን ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ እ- ኤ- አ- ) ገጽ ፩፻፲፩
7. ለምሳሌ ያህል ፡ የተሻሻለውን ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ- ም- የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቊ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ይ ለከቷል ።
8. አር ፡ ፒ ፡ ኤ ኮኔል ኢንተርናሺናል ሎው (፲፱፻፷፭ እ- ኤ- አ-) ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፰
9. ኤስ - ኤች- ፡ ከሳሽ ፡ ኤል- ሲኤች- ተከሳሽ ፤ በፓሪስ ፡ (ሬይሽስጊሪስት ፡ ጀርመን ፡ ፲፱፻፲፬ ፡ እ- ኤ- አ-)፥ እንትስይዱንግን ፡ ዴስ ፡ ራይሽስጌሪስትስ ፡ ኢን ፡ ዚቤልዘበን ፡ ቦልዩም ፡ ፹፭ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፬ ፡ አር ስታንገር ፡ ማትሪያልስ ፡ ኦን ፡ ፓብሊክ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ውስጥ ፡ እንደተጻፈ ፡ (፲፱፻፷፭ ፡ እ ፡- ኤ ፡ አ ፡ ያልታተመ ፡ በቀ- ኃ- ሥ- ዩኒቨ- የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ገጽ ፡ ፬፻፺፮ ።

የዚህን ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ቀላል ፡ ምሳሌ ፡ በመውሰድ ፡ ለመረዳት ይቻላል ። በሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ቢደረግና ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ የቀረጥና ፡ የታሪፍ ፡ አከፋፈል ፡ ደንቦችን ፡ ቢያሻሽል ፡ እነዚህም ፡ ደንቦች ፡ በሕግ ፡ ጸንተው ፡ ቢወጡ ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ ፈረሰ ፡ ተብሎ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ላይፋቁ ፡ ይችላሉ ። አለበለዚያ ፡ የውሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነት ፡ እንደ ተፈጸመ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚመለከተው ፡ ማንኛውም ፡ የአገሪቷ ፡ ሕግ ፡ እንዳልነበረ ፡ ይሆናል ። እነዚህ ፡ ከአንድ ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የተዛመዱ ፡ ደንቦች ፡ ውሉ ፡ ውጤት ፡ የሌለው እንደሆነ ፡ ወዲያው ፡ ውጤት ፡ የሌላቸው ፡ የሚሆኑበትንና ፡ የማይሆኑበትን ፡ ጊዜ ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችል ፡ ጠቅላላ ፡ መምሪያ ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። እያንዳንዱ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ በየግሉ ፡ መመርመር ፡ አለበት ። የያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መለየት ፡ አግባብ ፡ ያለውንም ፡ ሕግ ፡ ይለውጠው ፡ ይሆናል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚያገለግል ፡ ጠቅላላ ፡ መምሪያ ፡ በመፍጠር ፡ ፈንታ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በመመልከት ፡ የሚነሱትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ብቻ ፡ መመለስ ፡ ነበረበት ። በዚህ ፡ የትሪንጋሊን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ የተለየ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየትና ፡ ፅንሰ ፡ አሳቡን ፡ የተጠቀመበት ፡ ዘዴ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ። ስምምነቱ ፡ ስለተሻረ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻፵፯ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ይሆናል ፤ ሕጉ ፡ ወደ ፡ ውሉ ፡ የሚመራ፡ በመሆኑ ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ የሕጉንም ፡ መሰረዝ ፡ ያስከትላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

የጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉና ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ የተያያዙት ፡ ደንቦች ፡ የተሰረዙ ፡ በመሆናቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋብቻውን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ እንዳልነበረ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆጠርና ፡ የአስመራ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እንዲታረም ፡ አዘዘ ።

የጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማይ ውል ፡ ውድቅ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ አከራካሪ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያስነሳው ፡ የጋብቻው ፡ "እንዳልነበረ" ፡ ሆኖ ፡ መወሰድ ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አባባል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ጋብቻ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ እንዳልተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ፡ የሚል ፡ ከሆነ ፡ ሁለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ውጤቶች ፡ ይፈጠራሉ ። አንደኛ ፡ ስምምነቱ ፡ ውድቅ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸሙ ፡ የኤርትራ ፡ ጋብቻዎች ፡ ሁሉ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ ጋብቻው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ረገድ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ለምሳሌ ፡ አንዱ ፡ ያገባው ፡ ሰው፡ ኑዛዜ ፡ ሳይሰጥ ፡ ከሞተው ፡ ባለቤቱ ፡ ይዞታ ፡ ሥር ፡ የነበረውን፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የመውረስ ፡ መብት ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለውም ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ውጤቶች ፡ የሚያጠራጥሩ ፡ ሲሆኑ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ እና ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ እንደተፈጸመ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጸናው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ እናገኛለን ። በዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ የጋብቻቸውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከፈጸሙ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ቢመዘገብ ፡ ባይመዘገብ፡ ጋብቻው ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።[10] ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ አከራካሪው ፡ ነገር

10. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፭፻፸፯ ፡ ፭፻፸፱ ፡ ፯፻፭ ፡ ፯፻፲፯ ።

ውሉ ፡ የጸና ፡ ከሆነ ፡ ኃብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፡ ወይ ፡ የሚለው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አባባል ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ሲሆን ፡ ያመጣው ፡ ውጤት ፡ ግን ፡ ትክክለኛ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ብቻ ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ በመመርመር ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ በውስጣዊ ፡ ሕግ ፡ የሚያስከትለውን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ለሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ለሌላ ፡ ጸሐፊ ፡ ትቶታል ።